# ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ተግባራዊነት…

*ዮኒያስ 09-01-14*

የሰው ልጅ ወደዚህች ምድር ከመጣበት ዕለት ጀምሮ የሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች እንዳሉ እሙን ነው፡፡ እነዚህ መሠረታዊ ፍላጐቶች ተሟልተውለት ሕይወቱን መምራት ሲጀምር ደግሞ ለሕይወቱ ሳንካ ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶች ሊያጋጥሙት ይችላሉ፡፡

እነዚህ ክስተቶች ተፈጥሯዊም ሆነ ተፈጥሮዊ ባልሆነ መንገድ የሰው ልጅን የዕለት ተዕለት የሕይወት መስመር በማወክ በጤናና በማህበራዊ መስተጋብር ብሎም በሀገር ደረጃ ጭምር የኢኮኖሚ ድቀትን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

ከዚህ ቀደም ከግለሰብ አልፎ ሀገርን ጉዳት ላይ መጣሉ እምብዛም ትኩረት አልተሰጠውም ነበር፤ አሁን ላይ ግን የዓለም ሙቀት መጨመርና የሀገራት በኢንዱስትሪ መስፋፋት እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ምጥቀት የረቀቀ እድገት ማምጣት የዚያኑ ያህል ለሰው ልጅ የጤና ቀውስ ምክንያት ሊሆን የሚችል ስለሆነ የአየር ንብረት ለውጥ የዓለም ሀገራትን ትኩረት የሳበ አሳሳቢ ርዕሰ ጉዳይ ከመሆን ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

አሁን…አሁን የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ እና ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት በቀላል የሚታይ ጉዳይ አልሆነም፡፡ ሀገራችን አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመተግበር ከፍተኛ ርብርብ የምታደርግበት ዋንኛ ጉዳይም የአየር ንብረት መዛባትን በማስቀረት ቀጣይነት እና ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገቷን አስጠብቃ ከማስቀጠል ጐን ለጐን በአየር ንብረት ለውጥ የሚከሰቱ ተፈጥሯዊም ሆነ ተፈጥሯዊ ያልሆኑ የጐንዮሽ ጉዳቶችን ለማስቀረት እንደሆነ ይታመናል፡፡

ዓለም እንደ አንድ መንደር እየታየች ባለችበት በአሁኑ ወቅት በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ትስስሮሽ ሀገራት የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን አጠናክረው እና ተሞክሮ ወስደው የዜጎቻቸውን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ብሎም የሀገራቸውን ኢኮኖሚ አሳድገው ከኃያላን ተርታ ለማሰለፍ ወይም ከዘመኑ ጋር እኩል በመራመድ በኢኮኖሚ ደረጃቸው የፈረጠሙ ሆነው ለመገኘት ዘርፈ ብዙ የልማት ውጥኖችን ለማሳካት ቀን ከሌት ሲደክሙ ይስተዋላል፡፡

በልማት ውጤታቸውም የሀገራቸው ስም ከፍ ብሎ እንዲጠራ ጥረት ሲያደርጉ ይታያል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ለእድገት በሚደረጉ በርካታ ጥረቶች ውጤትን የሚቀንሱ አሊያም የተፈለገውን ውጤት ለማግኘት የማያስችሉ የተለያዩ ተፈጥራዊ እና ተፈጥራዊ ያልሆኑ የልማት ሳንካዎች ይገጥማሉ፡፡ እነዚህን ሳንካዎች ለመቀነስ የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ተግባራዊ የማድረግ ተግባር በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት ተሰቶት እየተሰራበት ይገኛል፡፡

ዓለም ለዜጎች ጤንነት አደጋ ብሎም ተፈላጊውን የምርት መጠን ለማግኘት እንቅፋት እየፈጠረ ነው የተባለውን የአየር ንብረት ለውጥ እንዲከሰት የሚያደርጉት የሙቀት አማጭ ጋዞች በከፍተኛ ሁኔታ መለቀቅ ሰዎች ተስማሚ የአየር ፀባይ እንዳያገኙ ችግር እየፈጠሩ በመምጣታቸው ሀገራት ልዩ ትኩረት ሰጥተው ይህን የካርቦን ልቀት ለመቀነስ ሰፋፊ ፕሮጀክቶች ተቀርፀውለት በመተግበር ላይ ነው፡፡

የዓለም ሀገራት የተለያዩ ትላልቅ ጉዳዮችን አንስተው በሚነጋገሩበት መድረክ ላይ ሳይቀር አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር በመገንዘብ እንደ አንድ አጀንዳቸው አድርገው ሲመክሩበት ቆይተዋል፡፡ በፖሊሲዎቻቸው ውስጥም አካተው ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራበት አቋም የያዙበት ሁኔታ ታይቷል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ በከፍተኛ ደረጃ እንዲከሰት ከሚያደርጉት መካከል ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዙት ከግዙፍ ፋብሪካዎች የሚለቀቁ በካይ ጋዞች መሆናቸው ይጠቀሳል፡፡ የእነዚህ ግዙፍ ፋብሪካዎች መገኛቸው በአብዛኛው ባደጉ ሀገራት ላይ ይሁን እንጂ የችግሩ ተጐጂ ግን ሁሉም የዓለም ሀገራት ህዝቦች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም የጉዳቱ ገፈት ቀማሾች በኢኮኖሚያችን ያልበረታንና በማደግ ላይ የምንገኝ የአፍሪካ ህዝቦች ስለሆን ችግሩን የምንቋቋምበት ብሎም የምንካስበት መንገድ ሊፈጠርልን ይገባል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን የአየር ንብረት ለውጡን ለመቆጣጠር እኛም የራሳችንን አስተዋጽኦ በማበርከት የአረንጓዴ ኢኮኖሚን በትጋት ለመተግበር ጥረት ልናደርግ ይገባል ሲሉ ነበር የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በዓለም አቀፉ መድረክ የተከራከሩት፡፡

በተለያዩ የአለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ ይህንን ጉዳይ አንስተው ሲከራከሩ ቆይተው ባደጉ ሀገራት ዘንድም ተቀባይነት አግኝቶ የአለም ሥጋት የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተለውን የዝናብ ሥርጭት መዛባትና ሌሎችንም የችግሩ ማሳያዎች የገለጹት፡፡ በአየር ንብረት ለውጥ በተለያዩ ሀገራት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ሊከሰቱ እንደቻሉ የተለያዩ የጥናት ውጤቶችም ያረጋግጣሉ፡፡

ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በማራመድ ሀገራችንን ከአየር ንብረት ለውጥ ጥቃት ለመታደግና በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች በመደረግ ላይ ናቸው፡፡

በሀገራችን ከ2003 የካቲት ወር ጀምሮ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ሥልትን ለመተግበር ከሃያ የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤቶች የተወጣጡ ከሃምሳ የሚበልጡ ባለሙያዎች በሰባት የተለያዩ ዘርፎች ላይ ሥልቱን ማርቀቃቸው ይታወሳል፡፡

የረቂቁ መዘጋጀት ዓለማም የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ዝቅተኛ እንዲሆን በማድረግ ኢትዮጵያ ለተነሳችለት የዕድገት ጉዳና ሥኬት አንዳች አስተዋጽኦ ለማበርከት ነው፡፡

በሀገራችን አረንጓዴ ኢኮኖሚን በመገንባት በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት አንዷ ለመሆን ተነስታለች፡፡ የሀገራችን የትኩረት አቅጣጫዎች በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዷ ላይ እንደተቀመጠው ዕድገቷን አስጠብቃ ለማስቀጠል የግብርና ምርት በመጨመር የኢንዱስትሪ መሠረትን አጠናክሮ በማስቀጠል ብዛት ያላቸው ፋብሪካዎች ተገንብተው ስራ እንዲጀምሩ ለማድረግ ምቹ መደላድሎችን መፍጠር እና የውጭ ገበያን በማሳደግ የኢኮኖሚያችንን እድገት አስጠብቆ ማስቀጠል ነው፡፡

በአካባቢ እና ደን ጥበቃ ባለስልጣን አስተባባሪነት ከሚመራው 7 የተለያዩ የፌዴራል መስሪያ ቤቶችን ካሳተፈው ቡድን መካከል ጉዳዩ በዋናነት ይመለከተዋል ተብሎ ሰፊ ስራ እየተሰራበት የሚገኘው አንዱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸውን ችግሮች በውል ለይቶ መስራት እንዳለበት ጥብቅ አቋም ተይዞ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማትን እውን ለማድረግ እየሰራ ይገኛል፡፡ ሀገራችን በጉዳዩ ላይ በአፍሪካ በቀዳሚ ደረጃ ላይ የምትገኝ ሆና ተሞክሮዋን ለሌሎች ሀገራት ለማጋራት የሚያስችል አቅም እንዳላት የዓለም ኃያላን ሀገራት ሳይቀር ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ለአየር ንብረት ለውጥ መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከሚታሰቡት የሥጋት አካባቢዎች አንዱ ኢንዱስትሪ ስለሆነና ወደፊትም የሀገራችንን ኢኮኖሚ የሚመራው ኢንዱስትሪው ይሆናል ተብሎ ስለሚጠበቅ ትኩረቴን በኢንዱስትሪው ዘርፍ ላይ ላድርግ፡፡

ሀገራችን የፋብሪካዎች ተረፈ ምርት በምን ያህል ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲከሰት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመተግበር በምታደርገው ጥረት የመጀመሪያዋ እንደሆነች እና ሌሎችንም በጉዳዩ ዙሪያ እያነቃቃች ያለች ሀገር ናት፡፡

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ከኢንዱስትሪ ከሚወጣው ሦስት በመቶ አጠቃላይ የካርቦን ዳይኦክሳይድ መጠን ልቀት ማለትም ከሁለት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ውስጥ ከአጠቃላዩ የኢንዱስትሪ ልቀት 50 በመቶውን ወይም ግማሽ ያህሉን ድርሻ የሚሸፍነው የሲሚንቶ ምርት ነው፡፡ ከእርሱ ቀጥሎ 32 በመቶ ከማዕድን ማውጣት፤ ከዚያ ቀጥሎም 17 በመቶ ከጨርቃ ጨርቅና ከቆዳ ኢንዱስትሪዎች የጋዞች ልቀት ይመነጫል፡፡ ከብረታ ብረት፣ ከሌሎች የምህንድስና ሥራዎች፣ ማዳበሪያን ጨምሮ ከኬሚካል ኢንዱስትሪ፣ ከወረቀት፣ ከምግብ ዝግጅት የሚወጣው ከአጠቃላዩ የኢንዱስትሪ የሙቀት አማቂ  ጋዞች ልቀት ሁለት በመቶ ብቻ እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በአየር ንብረት የማይበገር የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ የአየር ንብረት ለውጥ ክትትል መርህ ግብር በመዘርጋት የሙቀት አማቂ ጋዞችን ቁጥጥር በማድረግ በታዳሽ የሀይል ምንጮች መጠቀም  የጉዳቱን መጠን ይቀንሰዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በተለይም ፋብሪካዎች በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ የሚፈጠረውን የአካባቢ ብክለት ተጽዕኖ ለመከላከልና የአረንጓዴ ኢኮኖሚን እውን ለማድረግ ምን መሥራት እንዳለባቸው የተለያዩ ወርክ ሾፖችን በማዘጋጀት ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እየከወነ ይገኛል፡፡

በተለይም የሲሚንቶ አምራች ፋብሪካዎች ላይ ልዩ ትኩረት ተደርጐ የፋብሪካዎች ባለቤቶች የሙቀት አማቂ ጋዞችን እንዴት መቆጣጠር እንደሚገባቸው እና በምን መልኩ

ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች ተከናውነዋል፤ ወደፊትም አጠናክሮ ለመሥራት ታቅዷል፡፡ የኢንዱስትሪ ዘርፍ እድገት በከፍተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡ በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ከሚፈጠሩ ሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ጋር ተያይዘው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሊገጥሙ ስለሚችሉ እንደሰለጠኑ ሀገራት ሁሉ ዘመናዊና ሀብት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝነት አለው፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የካርቦን ልቀትን በመቀነስ ተስማሚ የአየር ንብረት በመፍጠር ረገድ የበኩሉን ጥረት ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፤ ወደፊትም ይህን ጥረት አጠናክሮ ለመቀጠል እቅድ ይዟል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ በሰዎች ላይ በርካታ የጤና ተጽዕኖዎችን ያስከትላል፡፡ ህሙማንን በማብዛት ለሞት ይዳርጋል፤ እንደ ወባና ቢልሀርዚያ ያሉ በሽታዎችን የሚያስተላልፉ ነፍሳት የማባዛት፣ ከአየር ፀባዩ መለዋወጥ ጋር በተያያዘ ለምሣሌ ከጎርፍና ከድርቅ ጋር የተያያዙ እንደ ተቅማጥና ኮሌራ ያሉ በሽታዎችን እንዲጨምሩ ያደርጋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ በጎርፍ እና በኃይለኛ ዝናብ ምክንያት የሚከሰቱ የአካል ጉዳቶች፣ የሞት አደጋዎች፣ የአስም እና የተለያዩ የመተንፈሻ አካል ችግሮች እንዲሁም በምግብ እና በውኃ አቅርቦት ብክለት ምክንያት ከፍተኛ የሆነ የጤና ቀውስ በሰዎች ዘንድ ያስከትላል፡፡

በአየር ንብረት ለውጥ ጉዳት የሚደርስባቸው የሰው ልጆች ብቻ ሳይሆኑ በርካታ አዕዋፍ እና እፅዋቶችም የችግሩ ተጠቂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከምድረ ገጽ ሊጠፉ የሚችሉበት አጋጣሚም ሰፊ ነው፤ ስለዚህ በጋራ የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማትን ተግባራዊ እናድርግ፡፡